# የዶክተር ወዳጄነህ ሙግት ንኡድ ወይስ ስሑት? “ቅዱስ መጋባት” እንዳለ ሁሉ፣ “ቅዱስ መፋታት” አለን?

ከተስፋዬ ሮበሌ
**ወርኀ መስከረም** 2001 **ዓ.ም**

ይህ ጽሑፍ፣ "ጌሜም" በሚል ስያሜ የሚታወቀው መጽሔት፣ በወርኀ መስከረም 2001 ዓ.ም፣ "እኔ በዚህ ምድር ታርጃለሁ" በሚል ርእስ ዶ/ር ወዳጄነህ መሐረነ ለመጽሔቱ የሰጡትን ቃለ ምልልስ እንዲሁም መጋቢ ሙሉጌታ ግዛት፣ "ስለወዳጄነህ መናገር እችላለሁ" በሚል ርእሰ ያቀረቡትን ጽሑፍ በስፋት ለመመርመር ይሞክራል:: የእነዚህ ወገኖች ጽሑፍ እንዲሁም ይህ ግምገማ የሚያጠነጥነው፣ ዶ/ር ወዳጄነህ የቀድሞ ባለቤታቸው የሆኑትን ወ/ሮ አስቴር ደምሴን ፈተው አዲስ ጋብቻ መመሥረታቸው፣ ቃለ እግዚአብሔርን የተከተለ ነው ወይስ አይደለም በሚለው መሠረታዊ ጭብጥ ላይ ነው::

የቀድሞ ባለቤታቸውን ፈተው አዲስ ጋብቻ ያካሄዱት ዶ/ር ወዳጄነህ እንዲሁም የግለሰቡ መንፈሳዊ መምህር የሆኑት መጋቢ ሙሉጌታ፣ ፍቺው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዲሁም "በአምላክ ልዩ አሠራር" እውን የሆነ ክሥተት ነው የሚለውን ነጥብ ይዘው የተከራከሩ ሲሆን፣ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ የሆንሁ እኔ ደግሞ፣ ለፍቺው ምክንያት ተደርገው በእነዚህ ወገኖች የቀረቡት ሙግቶች፣ ፍቺው ትክክኛ መሆኑን የማያጸድቁ እንዲያውም ድርጊቱ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ገሓድ የሚያወጡ ናሙናዎች መሆናቸውን ለአንበብያን በውል ለማሳየት ሙከራ አደርጋለሁ:: በአጠቃላይ ይህ ጽሑፍ የዶ/ር ወዳጄነህ የፍቺ አካሄድም ሆነ መጋቢ ሙሉጌታ ፍቺውን ያጸደቁበት ምክንያት፣ ምን ያህል ሚዛን ይደፋል የሚለውን ጉዳይ ቃለ እግዚአብሔርንና ሥነ አመክንዮን መሠረት አድርጎ ይመረምራል:: ይህ ምርመራ የዶ/ር ወዳጄነህ የቀድሞ ባለበት ወ/ሮ አስቴር፣ በካሪዝማ መጽሔት ላይ የሰጡትን ቃለ ምልልስ መሠረትም ሆነ ታሳቢ የሚያደርግ አይደለም—ቢያንስ በአብዛኛው::

## ሙግት የማይቀርብባቸው ታሳቢ መሠረቶች

ይህ ጽሑፍ የሚከተሉትን ሦስት መሠረታዊ ነጥቦች ትክክለኛነታቸውን ከሙሉ ልብ በመቀበል ሙግቱን የሚያዋቅር ስለሆነ፣ እነዚህ መሠረቶች ትክክለኛ ናቸው ወይስ አይደሉም በሚለው ጉዳይ ላይ ማስረጃም ሆነ ሙግት በጭራሽ አያቀርብም:: ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት፣ የጽሑፌም ሆነ የዚህ መጽሔት ቀዳማይ ተደራስያን ክርስቲያኖች በመሆናቸውና ክርስቲያኖች ደግሞ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሦስት መሠረታዊ ነጥቦች ፈጸመውና ጨልጠው ስለሚቀበሉ ነው:—

፩. መጽሐፍ ቅዱስ አንዳችም ሕጸጽ/እንከን የሌለበት የእግዚአብሔር አፊዎተ/እስትንፋሰ ቃል ነው::

2. እውነት አንጻራዊ (relative/subjective) ምልከታ ሳትሆን ፍጹማዊ/ነባራዊ (objective) መሠረት ነች[1]፡፡ ለአስተምህሮቻችንም ሆነ ለምግባራችን መሠረት የሚሆኑ እውነቶች በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ ለትምህርታችን ተቀምጠውልናል፡፡
3. ሥነ አመክንዮ (Logic)፣ የሙግት አካሄዶችን የምንመረምርበት ትክክለኛ መሣሪያ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ከቃለ እግዚአብሔር ጋር የሚጣረስ ጉዳይ አይደለም፡፡

እነዚህ ሦስት መሠረታዊ ነጥቦች ትክክልኛ አይደሉም የሚል አቋም ያለው ሰው፣ በዚህ ጽሑፍ የሙግት አካሄድም ሆነ በሚደርስበት ድምዳሜ ላይስማማ ይችላል፡፡ ስለዚህ ይህ ጽሑፍ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸውን ሦስት መሠረታዊ ነጥቦች መሠረት ያደረገና ለክርስቲያኑ ማኅበረሰብ የተጻፈ ጽሑፍ ነው፡፡

## የዚህ ጽሑፍ ዐቢይ ዐላማ

ይህን ጽሑፍ ለመጻፍ ያነሣሣኝና የጽሑፌ ዐላማ የሚከተሉት አምስት መሠረተ ነጥቦች ናቸው:—

1. አንባብያን በተለይ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ይህን መሰል አወዛጋቢ ርእስ ጉዳይ በሚገጥመው ጊዜ ቃለ እግዚአብሔርንና ሥነ አመክንዮን (Logic) ማዕከል ባደረገ መልኩ ምርመራውን እንዴት ማካሄድ እንደሚገባው ለማስተማር፣
2. ክርስቲያኖች ጋብቻ አምላክ ሠራሽና ክቡር ተቋም መሆኑን ተገንዝበው ለዚህ ክቡርና አምላክ ሠራሽ ተቋም ተገቢውን ስፍራ እንዲሰጡ ለማሳሰብ (“እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው” ማቴዎስ 19÷6፤ ማርቆስ 10÷9) ፡፡
3. ጋብቻ መፍረስ የሚችለው በሞት ብቻ ስለሆነ፣ ክርስቲያኖች በቅዱስ ጋብቻ ራሳቸውን ወስነው እንዲኖሩ ጥሪ ለማቅረብ (ማቴዎስ 22÷23-33 ላይ ጋብቻ ከተጣማሪዎቹ ወገኖች መኻል አንዱ ቢሞት ቢለይ ከብቻው እንደሚፈርስና በመለቲቱም ሆነች ባልየው ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መፈጸም እንደሚችሉ ያስተምራል፡፡ በነገረ መለኮት ምሁራን ዘንድ የሚያወዛግበው ጉዳይ ከሞት በስተቀር ጋብቻን የሚያፈርሰው ጉዳይ አለን? የሚለው ርእሰ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ከሞት በስተቀር ፍቺን ለማካሄድ በምክንያትነት የሚቀርበው ደግሞ የዝሙት ጉዳይ ብቻ መሆኑን ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ መረዳት ይኖርበታል)[2]፡፡
4. የዶክተር ወዳጄነህ ወዳጆች፣ ባልንጀሮችና አድናቂዎች እኚህ ግለሰብ ጋብቻቸውን ለማፍረስ የሄዱበት ጐዳና ፍጹም የተሳሳተ መሆኑን ተገንዝበው ራሳቸውን ከመሰል ድርጊት እንዲጠብቁ ለማሳሰብ፣
5. እኩይ ምግባራቸውን በብልጣብልጥነት ለማጽደቅ የሚፈልጉ ግለሰቦች (በተለይ ደግሞ የወንጌል አገልጋይ ነን የሚሉ ሰዎች) "ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ተላላ ነው፤ የሚሰጡትን ሁሉ በእልልታና በሆታ ይቀበላል" የሚለውን አስተሳሰብ እርግፍ አድርጎ በመተው፣ ለፈጸሙት

---

[1] ግብረገብ አንጻራዊ ወይስ ፍጹማዊ በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ፣ *የሥነ ምግባር መርሖ* (ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ 1996 ዓ.ም) በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል፤ በተለይ ገጽ 43-92፡፡

[2] ፍቺንና ደግም ጋብቻን በተመለከተ አንባብያን ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ ምኒልክ አስፋው፤ *ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ርእሰ ጉዳዮችና ተግዳሮቶች* (ሮሆቦት ማተሚያ ድርጅት፤ 1999 ዓ.ም) ከገጽ 136-167 ይመለከቷል፡፡

ኀጢአት በንጹሕ ልብ በይፋ ንስሓ መግባትን የኑሮ መስመራቸው አድርገው እንዲከተሉ ለማሳሰብ ነው።

# I. በግለሰቦች አስተምህሮም ሆነ ምግባር ላይ ሒስ መዘንዘር ትክክል ነውን?

ክርስቲያኖች ይህ እኔ አሁን የጻፍሑትን ዐይነት ጽሑፍ እንዳይጽፉ ወይም በመሰል ርእሰ ጒዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት በማካሄድ እውነቱን ከከውሸት እኩዩን ከሠናይ እንዳይለዩ እክል የሚፈጥሩ አንዳንድ አስተሳሰቦች በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ዘንድ ስላሉ፣ በቅድሚያ እነዚህን የክልከላ መሰናክሎች በመጽሐፍ ቅዱስ እየመዘንን ከመንገድ ልናወጣቸው ይገባል። ቅዱሳት መጻሕፍት ሥነ ምግባራዊ አካሄዶችንም ሆነ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን ያለ አንዳች ማመንታት፣ በጥንቃቄ እንዲሁም በሙሉ ልብ እንድንመረምር አበክረው ቢያስገነዝቡም (ዘዳግም 13÷1-5፤ 18÷20-22፤ ሐዋርያት ሥራ 17÷11፤ 2ጴጥሮስ 2÷1፤ 3÷2፤ 1ዮሐንስ 4÷1-2፤ ይሁዳ 17)፣ ይህን አምላካዊ ትእዛዝ ከሙሉ ልባችን ተግባራዊ እንዳናደርገው ልባችንን ሸብበው አፋችንን ለጒመው የሚይዙ ዘመን ያፈጁ በርካታ ጥያቄዎች አብረውን አሉ። ለእነዚህ ጥያቄዎች (ቢያንስ ዋና ዋና ለሚባሉት) አጥጋቢ መልስ ማፈላለግ ካልቻልን፣ ቃለ እግዚአብሔር "መርምሩ" ሲል የሰጠንን ትእዛዝ ተግባራዊ ልናደርገው አንችልም። ይህም ጽሑፍ ለአንባብያን አሳውቀዋለሁ የሚለው ርእሰ ጒዳይ የተተለመለትን ግብ ከዳር ማድረስ አይችልም። ስለዚህ ከዚህ በመቀጠል ከበርካታ ሰዎች አፍ ተዘውትረው ለሚሰሙ የምርመራ ማነቄዎች መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ።

## በሌሎች ሰዎች ምግባር ላይ ሒስ መሰንዘር ትክክል አይደለምን?

"አንተ ማን ነህና ነው የሌላውን ምግባር የምትተቸው?" የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፤ ተገቢ ጥያቄ ነው፤ ተገቢ መልስም ሊፈለግለት ይገባል። በሌሎች ሰዎች ምግባርም ሆነ አስተምህሮ ላይ መፍረድ/ሒስ መሰንዘር ትክክል የማይሆንባቸው ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው:— (1) ርእሰ ነገሩን በጥልቀት ያልመረመረ ፍርድ ትክክል አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ በመልክ አትፍረዱ" (ዮሐንስ 7÷24) የሚለው አነጋገሩ፣ ማናቸውንም ዐይነት ፍርዶችን የሚኰንን ሳይሆን፣ ፍርዳችን ምን ላይ ማነጣጠር/ትኵረት ማድረግ እንደሚገባው የሚያስጠነቅቅ ነው። በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ትክክል አይደለም ያለው ፍርድ፣ ገጽታን በመመልከት ብቻ የሚካሄደውን ፍርድ ነው። ይኸውም ግልብ በሆነ ሁኔታ፣ የጒዳዩን ገጽ በመመልከት ብቻ ርእሰ ነገሩን በጥልቀት ሳይመረምሩ የሚካሄደውን ፍርድ ማለቱ ነው። (2) ግብዝነት የሞላበት ፍርድ ትክክል አይደለም (ማቴዎስ 7÷1-5፤ 23÷1-3)። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ከጠማማ ልብ ተነሥተው የሚያደርጉትን ማናቸውም ነገር እግዚአብሔር ለበጎ ሊጠቀምበት ስለሚችል፣ ጠማማ ልብ ያላቸው ሰዎች እንኳ ሒስ ቢሰነዝሩብን በእነርሱ ማንነት ላይ ሆነን ሒሱን መመልከት ሳይሆን፣ ሒሱ በራሱ ትክክል ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጒዳይ ትኵረት ሰጥተን ልንመረምረው ይገባል (ፊልጵስዩስ 1÷15-18)።

በሌሎች ሰዎች ምግባርም ሆነ አስተምህሮ ላይ መፍረድ/ሒስ መሰንዘር ትክክል የሚሆነው፣ ሒሱ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ሲያደርግ ብቻ ነው። ሰባክያን ነን፣ የወንጌል አስተማሪዎች

ነን፣ ዘማሪያን ነን፣ ነቢያት ነን፣ መምህራን ነን የሚሉ ሰዎች ትክክልኝነታቸው የሚረጋገጠው፣ አስተምህሮአቸው ከክርስቶስ ሐዋርያትና ነቢያት ትምህርት ጋር ተነጻጽሮ ትክክል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው (ሐዋርያት ሥራ 17÷11፤ 2ጴጥሮስ 2÷1፤ 3÷2፤ 1ዮሐንስ 4÷1-2፤ ይሁዳ 17)። የትምህርቱን ትክክልኝነትም ሆነ ስሕተት በትክክል ከተረዳን ደግሞ፣ ትክክለኛውን ትምህርት ትክክለኛ፣ የተሳሳተውን ደግሞ የተሳሳተ ማለት እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል (ሮሜ 12÷2:9፤ 1ቆሮንቶስ 12÷10፤ 14÷29፤ 1ተሰሎንቄ 5÷19-22)። ይህ ብቻ አይደለም በቃለ እግዚአብሔር ሚዛን ነገሮችን መርምረን፣ በሥነ ምግባርም ሆነ (ማቴዎስ 18÷15-18፤ 1ቆሮንቶስ 5÷9-13) በአስተምህሮ (ሮሜ 16÷17፤ ገላትያ 1÷6-9፤2ጢሞቴዎስ 3÷16-4÷4፤ ቲቶ 3÷10-11) ስተው የተገኙትን ሰዎች ከስሕተታቸው እንዲመለሱ፣ ጊዜ ሰጥተን ማስተማርና መምከር ይኖርብናል። ከጥመታችን አንመለስም የሚሉ ከሆነ ግን፣ ቢያስፈልግ ስማቸውን በመጥቀስ ደርጊታቸውንም ሆነ ትምህርታቸውን ማውገዝ እንደሚያስፈልግ ቃለ እግዚአብሔር በግልጽ ያስተምራል (እባክዎን እነዚህን ክፍሎች ያንብቡ 2ጢሞቴዎስ 2÷17፤ 2÷17)። ከእንዲህ ዐይነቱ ሰውም ጋር ኅብረት እንዳናደረግ መጽሐፍ ቅዱስ በብርቱ ያስጠነቅቃል፣ “መከፋፈል የሚያመጣን ሰው አንድ ጊዜ ምከረው፤ ለሁለተኛ ጊዜ አስጠንቅቀው፤ ከዚያ ካለፈ ከእርሱ ጋር አንዳች ነገር አይኑርህ። እንዲህ ዐይነቱ ሰው የሳተና ኀጢአተኛ ነው፤ ራሱንም እንደሚኰንን ዕወቅ” (ቲቶ 3÷10-11)።

## “እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ” ማለት ምን ማለት ነው?

“ሰዎች ሁሉ በቃለ እግዚአብሔር ይመዘኑ” የሚለውን እውነት ታሳቢ በማድረግ፣ የአንዳንድ ግለሰቦችን ወይም ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮና ምግባር ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርገን ትምህርታቸውን፣ ምግባራቸውን ወይም ዝማሬአቸውን ስናሒስ ብዙ ሰዎች፣ “እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ” የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በመጥቀስ፣ ሒሳችንን ከጅምሩ ያጣጥሉታል። እነዚህ ሰዎች ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በመጥቀስ ሊያስተላልፉ የፈለጉት መልእክት፣ “በእነዚህ ልዩ የእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ሒስ መሰንዘር የሚችለው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው” የሚለውን ሐሳብ ነው። ይህ ሐሳብ ትክክል ነው ወይስ ትክክል አይደለም የሚለውን ጉዳይ የምንመረምረው፣ “እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ” የሚሉትን ክፍሎች በቅርበት በመመርመር፣ የክፍሎቹን ትክክለኛ ትምህርት ከእነዚህ ሰዎች ሐሳብ ጋር በማነጻጸር ብቻ ነው። “እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ” የሚሉት ምንባባት የሚገኙት፣ በሚከተሉት ሁለት ክፍሎች ላይ (1ዜና 16÷22፤ መዝሙር 105÷6-14) ሲሆን፣ በምንባቡ ውስጥ፣ “የተቀቡ” የተባሉትም ሰዎች ርእሳን አበው ማለትም አብርሃም፣ ይስሐቅና ያቆብ ናቸው። የነገረ መለኮት ምሁራን እነዚህ ሰዎች “የተቀቡ” የተባሉበት ምክንያት፣ ቃለ እግዚአብሔር እንዲሁም የእግዚአብሔር ኪዳን በመጀመሪያ ወደ እስራኤል የመጣው በእነዚህ ሰዎች አማካይነት ስለሆነ ነው የሚል አስተያየት አላቸው። “የተቀቡ” የሚለው ቃል፣ “ነቢይ” የሚለውን ቃል እንደሚያሳይ ከዐውዱ በግልጽ መመልከት ቢቻልም፣ እነዚህ ሰዎች ግን ከነቢይ በላይ እንደ ሆኑ መገንዘብ ይኖርብናል፤ ምክንያቱም የእነርሱ ዝርያዎች የከነዓንን ምድር እንደሚገዟት እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋልና (መዝሙር 105÷11፤ ዘፍጥረት 17÷6:16፤ 35÷11)። ይሁን እንጂ ይህ አገላለጽ በመጽሐፍ ቅዱስ እምብዛም የተለመደ አይደለም (1ነገሥት 19÷16፤ ኢሳይያስ 61÷1)። ብሉይ ኪዳን “በእግዚአብሔር የተቀባ” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው፣ (ቢያንዝ በአብዛኛው) ለእስራኤል ነገሥታት ብቻ ነው

(ለምሳሌ 1ሳሙኤል 2÷10:35፤ 16÷12-13፤ 2ሳሙኤል 1÷14:16፤ መዝሙር 2÷2፤ 89÷38:51፤ ዳንኤል 9÷25:26፤ 1ዜና 11÷3፤ 14÷8፤ 29÷22፤ ኢሳይያስ 45÷1)። ከእነዚህ ምንባባት በግልጽ የምንረዳው እውነት፣ በእግዚአብሔር የተቀቡ የተባሉት ሰዎች በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበራቸው ሰዎች ናቸው እንጂ መምህራን፣ ሰባኪያን፣ ወንጌላውያን ወዘተ አይደሉም። አንዳንድ ሰዎች በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ልዩ በሆነ ሁኔታ የሚጠቀምብኝ ልዩ ሰው ነኝ ስለሚሉ፣ በዚህ የማዕረግ ስም ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያቀርባሉ። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ያልተገነዘቡት መሠረታዊ ነጥብ፣ እግዚአብሔር እነዚህን የተቀቡ ሰዎች አትመርምሩአቸው ወይም አታሒሷቸው ያለማለቱን ነው። ለምሳሌ በዘፍጥረት 20÷7 ላይ እግዚአብሔር ሣራን ለአብርሃም እንዲመልስ ለጌራራው ንጉሥ ለአቤሜሌክ ባስጠነቀቀው ጊዜ፣ እግዚአብሔር የአብርሃምን ነቢይነት መስክሮአል። ነገር ግን አብርሃም ነቢይ መሆኑ አቤሜሌክ የአብርሃምን ውሸት መርምሮ እንዳይረዳ አላገደውም (ቍጥር 9-10)። አንድ ሰው የእግዚአብሔር ነቢይ ነኝ እያለ፣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምግባር የሚየሳይ፣ የተሳሳተ ዶክትሪን ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ትንቢት የሚያስተላልፍ ከሆነ፣ ይህን ሰው እንዳንቀበለው እንዲያውም እንድናወግዘው ቃለ እግዚአብሔር ያስተምረናል (ዘዳግም 13÷1-5፤ 18÷20-22)። ሐዲስ ኪዳን፣ ክርስቲያኖች **ሁሉ** እንደ ተቀቡ በግልጽ ያስተምራል (2ቆሮንቶስ 1÷21)። ስለዚህ ተቀብተናል በሚል ሒሳብ፣ ከቅዱሳት መጽሐፍት ትምህርት ጋር የሚቃረን ወይም በብሉያትና በሐዲሳት የሌለ ትምህርት የሚያስተምሩትን ሰዎች ትምህርት ያላንዳች ማቅማማት ወግድ ልንለው ያስፈልጋል (ገላትያ 1÷6-9)። በክርስቶስ ያገኘነውን ዐርነት የሚቃረን ነውና (1ዮሐንስ 2÷20:27)። ሐዲስ ኪዳን የሐሰት መምህራን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልከው እንደ ገቡ በግልጽ የሚያስተምርበት ሁኔታ (ሮሜ 16÷17፤ 1ጢሞቴዎስ 1÷3፤ ቲቶ 1÷11፤ 3÷10-11) "የተቀባሁ ሰው ነኝ"፣ "ማንም ትምህርቴን ወይም ትንቢቴን ወይም ደግሞ ዝማሬዬን ሊመረምር አይገባም" በማለት ከቃለ እግዚአብሔር ጋር የሚጋጭ ትምህርት ማስተማር ፈጽሞ ውጉዝ ነው። ተቀብተናል የሚሉ ሰዎች መቀባታቸውን ማሳየት ያለባቸው ትምህርታቸውም ሆነ ምግባራቸው እንደ ቃለ እግዚአብሔር መሆኑን በግልጽ በማሳየት፣ ሰዎችም መርምረው ይህ ጉዳይ እውነት መሆኑን እንዲያውቁ በማድረግ ብቻ ነው።

## "መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው የወሰድሁትን እርምጃ መመርመር አይችልም፤ ድርጊቴ አልገባ ካለህ ጸልይ እንጂ አትፍረድ" ማለት ትክክል ነውን?

አንዳንድ ሰዎች፣ "እኔ የምሄድበት የሕይወት አካሄድ፣ የማስተምረው ትምህርት ወይም የምዘምረው መዝሙር መንፈሳዊነቱ እጅግ ጥልቅ ስለሆነ፣ የትምህርቴ ወይም የዝማሬዬ ጭብጥ አልገባ ካላችሁ፣ እግዚአብሔርን በጾምና ጸሎት ጠይቁት እንጂ፣ በትምህርቱ ላይ አትፍረዱ" ይላሉ—ከፈረድን ግን ቅሥፈት እንደሚጠብቀን።

ይህ ዐይነቱ የአትመርምሩኝ ክልከላ ቢያንስ ሦስት መሠረታዊ ችግሮች አሉበት። **አንደኛ፤** ትምህርታቸው በመንፈሳዊ ይዘቱ የቱንም ያህል ጥልቅ ቢሆን፣ መሠረታዊ ከሚባሉት ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ጋር መጋጨት የለበትም[3]። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል እርስ

---

[3] ከተነሣንበት ርእሰ ጉዳይ ጋር በተዛመደ መልኩ ቃለ እግዚአብሔር ፍቺ መፍረስ የሚችለው በሞት ብቻ እንደ ሆነ በግልጽ በሚያስተምርበት ሁኔታ በማናቸውም ዐይነት መልኩ ፍቺ መፈጸም ውጉዝ እጅግ ውጉዝ ነው።

በርሱ የሚቃረን አይደለምና። ስለዚህ ትምህርታቸው ዐበይት ከሚባሉት እንዲሁም በግልጽ ከተቀመጡት ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ጋር ምን ያህል ይጣጣማል የሚለው ጉዳይ የግድ ሊተኰርበት የሚገባው ጉዳይ ነው። **ሁለተኛ፤** ቃለ እግዚአብሔር “እጅግ ምስጢር” የሚለው፣ ለዘመናት ተሰውሮ የቆየውን የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው የመሆን ጉዳይ ነው። ይህ እውነት እንኳ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ይፋ አድርጐታል። ይህም ምስጢር ለዘመናት ተሰውሮ የነበረ፣ አሁን ግን ተገልጦ በይፋ የሚሰበክ መለኮታዊ እውነት ነው፣ “ይህም ቃል ከዘመናትና ከትውልዶች ተሰውሮ ምስጢር ሆኖ ቈይቶ ነበር፤ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል” (ቈላስይስ 1÷26፤ እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ሮሜ 11÷25፤ 16÷25፤ ኤፌሶን 1÷9፤ 3÷3:4:6:9፤ 5÷32፤ 6÷16፤ ቈላስይስ 1÷27፤ 2÷2፤ 4÷3፤ ራእይ 10÷7)። ስለዚህ በክርስቲያናዊ አስተምህሮ ውስጥ ይፋ ያልወጣ ወደ ፊት ይፋ የሚሆን ምስጢር አለ ማለት ስሕተት ነው።

**የ**ብሉያትም ሆነ የሐዲስ ኪዳን ቀኖና የተዘጋው፣ ለድነት የሚሆነን ማናቸውም ዐይነት ዕውቀት/እውነት በእግዚአብሔር ጸጋ በቃሉ ውስጥ ይፋ ስለተደረገልን መሆኑን ልብ ይሏል። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ መጽሐፍ ስለሆነ፣ እግዚአብሔር የቃሉን ትርጕም ለልቡናችን እንዲያበራ በፊቱ በትሕትና በመቅረብ ጸሎት ማድረስ እንደሚገባን ከሙሉ ልብ የምንቀበለው ጉዳይ ቢሆንም፣ የግለሰቦችን አስተምህሮ ለመረዳት ሱባኤ መግባት/አበክረን መጸለይ አይኖርብንም። መጸለያችን የግድ ሆኖ እንኳ ቢገኝ፣ ከጸሎቱ በኋላ ትምህርቱን እንዲገመገም መፈቀድ ይኖርበታል። በጸሎትና በቃሉ የተጉ ወገኖች በትምህርቱ ላይ ፈጣን ግምገማ ቢያቀርቡ፣ “አልጸመም አልጸለየም” በሚል ብቻ ሒሳቸው ውድቅ ሊደረግ አይገባውም። ውድቅ መሆን ካለበት ውድቅ የሚሆነው የሁለቱም ወገን ማስረጃ (የተገምጋሚውም ሆነ የገምጋሚው) በሰከነ ሁኔታ ከተመረመረ በኋላ ነው። **ሦስተኛ፤** ቃለ እግዚአብሔር ሃይማኖታዊ ትምህርቶችንና ምግባሮችን **ሁሉ** እንድንፈትን ያስጠነቅቃል (ዘዳግም 13÷1-5፤ 18÷20-22፤ ሐዋርያት ሥራ 17÷11፤ 2ጴጥሮስ 2÷1፤ 3÷2፤ 1ዮሐንስ 4÷1-2፤ ይሁዳ 17)። ይህ ጉዳይ ደግሞ **ሁሉን** የምንፈትንበት ቃል (ሚዛን) እንደ ተሰጠን ታሳቢ ያደረገ ነው።

## II. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍቺና ዳግም ጋብቻ ምን ያስተምራል?

**የ**ውይይታችን መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሆነ፣ በርእሰ ጉዳዩ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ትምህርት ምን ይመስላል የሚለውን ጉዳይ በአጭሩ መከለስ ለውይይታችን ጥሩ መደላድል እንደሚሰጥ በማሰብ ቃለ እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ ስለ ፍቺ የሚያስተምረውን ትምህርት በአሰሳ መልክ ለማየት ሙከራ እናደርጋለን[4]። ትዳር አምላካዊ ተቋም ይሁን እንጂ ብርቱ ትግል በአንጻሩ ደግሞ ታላቅ ደስታ የሚገኝበት አምላካዊ ጥምረት ነው። ባልና ሚስት ከተለያየ የሕይወት ተሞክሮ የተገኙ፣ የተለያየ ፍላጎት፣ ተሰጥኦና ክህሎት የተቸራቸው፣ የአስተሳሰብ አድማሳቸው ሊለያይ የሚችል ሰዎች እንደ መሆናቸው መጠን፣ "አንድ አምሳልና አንድ አካል" ሆነው ለመኖር ሲነሡ ትልቅ ፈተና እፊታቸው እንደ ሚጋረጥ እሙን ነው። ይህ ፈታኝ ትግል የጋብቻን ክቡርነት የሚያደምቀው ከሆነ እንጂ የሚያጠፋውም ሆነ የሚያደበዝዘው

[4] ከዚህ በታች ያለው ሐሳብ የተወሰደው ወንድም ምኒልክ አስፋው፤ *ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ርእሰ ጉዳዮችና ተግዳሮቶች፤* (ሮሆቦት ማተሚያ ቤት፤ 1999 ዓ.ም), 136-167 በሚል ርእስ ካዘጋጀው መጽሐፍ ነው። በርእሰ ጉዳዩ ላይ ሰፊ ማብራሪያ የሚፈልጉ ሰዎች ይህን መጽሐፍ እንዲያነቡ ከልብ አበረታታለሁ።

አይደለም፡፡ ሰዎች ይህን ፈተና በድል ማለፍ የሚችሉት የጋብቻ ጀማሪና ፈጻሚ በሆነው በልዑል እግዚአብሔር እርዳታ ብቻ እንደ ሆነም ልብ ይሏል፡፡ በእልኸኝነት አንዱ ወደ ግራ ሌላው ወደ ቀኝ እጓዛለሁ የሚል ከሆነ ግን ትዳሩን የሚሸረሽሩትና ትዳሩን የሚያፈርሱት አያሌ ምክንያቶች መከሠታቸው አይቀርም፡፡

በአገራችን ለትዳር የሚሰጠው ግምት ትልቅ እንደ ሆነ ይታወቃል፡፡ ባንጻሩም መፋታት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የተወገዘ ምናልባት የተጠላ ተግባር ነው፡፡ ከጥቂት ዓመታት በተለይም ከአንድና ሁለት ዐሠርታት ወዲህ በአገራችን በተለይም በከተሞች አካባቢ ለትዳር የሚሰጠው ግምት እየወረደ፣ ለፍቺ የሚሰጠው ስፍራ እየላቀ መጥቷል፡፡ ከዓመታት በፊት ኅብረተሰቡ ሲያወግዛቸው የነበሩ ተግባሮች ዛሬ ማንም አያፍርባቸውም፡፡ ጥናት አልተደረገበትም እንጂ በየዓመቱ ከሚፈጸሙ ጋብቻዎች መካከል ብዙዎቹ እንደሚፈርሱ ምንም ጥርጥር የለውም[5]፡፡ ጉዳዩ ጥናት ተደርጎበት ትክክለኛው አኀዝ ባይታወቅም፣ በየኀዳናውና በየሕፃናት ማሳደጊያው የምናያቸው ሕፃናት የዚህ ችግር ውጤት እንደ ሆኑ ለመገመት ከባድ አይደለም፡፡ ጥብቅ የነበረው ባህላችን እየወደቀ መምጣቱን ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ በተለይም ምግባራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የነበረን ጥብቅነት ፍጹም ተንዷል ቢባል እንደ አጉል ኮናኝ አያስቈጥርም፡፡ ከዚህ በፊት ያልሰማናቸው ብሂሎች፣ ያላየናቸውም መርሖች እየወረሩን  ይገኛሉ፡፡ እና እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን በትልቅ ፍጥጫ ውስጥ ናት ማለት ነው፡፡ በመሆኑም መፋታትንና እንደገና መጋባትን አስመልክቶ ቤተ ክርስቲያን ነገረ መለኮታዊና ምጋቤአዊ መልስ መስጠት  ይኖርባታል፡፡ እርግጥ ነው መፋታት ብዙ ውስብስብ ጉዳዮች አሉበት፡፡ ይሁንና ጉዳዩ የቱንም ያህል ውስብስብነት ቢኖረውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ ግን ይሻል፡፡ ታዲያ አወዛጋቢነቱም እንዳለ ሆኖ ነው፡፡

ጌታ ኢየሱስ መፋታትን አስመልክቶ የተናገራቸው ቃሎች ብዙ አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ታዲያ አንድ ነገር ልብ ማለት አለብን፡፡ ይኸውም ጌታ በተናገራቸው ቃሎች ላይ ብዙ አስተያየት ቢሰነዘርም፣ ሁሉንም ግን አንድ የሚያደርጋቸው ሐሳብ አለ፡፡ ሁሉም ሐታትያን ኢየሱስ መፋታትን የሚያየው እንደ ትልቅ ውድቀት እንደ ሆነ ይስማማሉ፡፡ መፋታት የእግዚአብሔርን ዐላማ (የመጀመሪያ ሐሳብ) እንደ መሳት ይቈጠራል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር በትዳር ያጣመራቸው ሰዎች መለያየት (መፋታት) የለባቸውም፡፡ በመሆኑም "ቅዱስ መጋባት" እንደሚባለው ሁሉ "ቅዱስ መፋታት" የሚባል ነገር የለም፡፡ አዲስ ኪዳን "መፋታትንና እንደገና መጋባትን" በተመለከተ የሚሰጠን ትምህርት በይዘቱ የተለያየና ውስብስብ ቢሆንም፣ አንድ ወጥ ትምህርት ግን አለው፡፡ ይኸውም ጋብቻ አንድ ለአንድና ቋሚ ነው፤ ይህ መርሕ ወይም ግዕዝ (norm) በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጽኑ መሠረት አለው፡፡ ክርስቲያኖች ጋብቻን እንዲመለከቱት የተጠሩት **የደቀ መዛሙርነት** መገለጫ አድርገው  ነው፡፡ ይኸውም እነዚህ ጽሑፎች በተጻፉበት ባህላዊ መቼት ውስጥ መፋታት አንዱ አማራጭ (ቢያንስ ለባሎች) ተደርጎ ቢወሰድም የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የሆኑ ሁሉ ግን መፋታትን እንዲያወግዙ

---

[5] በአሜሪካን አገር ከሚፈጸሙ ሁለት ጋብቻዎች መካከል አንዱ ይፈርሳል፡፡ ለምሳሌ እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ1988 ዓ.ም ብቻ 2,389,000 ሰዎች ተጋብተው ነበር፤ በዚሁ ዓመት 1,183,000 ሰዎች ተፋተዋል፡፡ ይህም ማለት በየዓመቱ የሚጋቡ ሰዎችን ያህል ይፋታሉ ማለት ነው (Klyne Sondgrass, *Divorce and Remarriage*. Chicago: Covenant publication), 1.

ተጠርተዋል፡፡ መፋታት በአገራችን ብቻ ሳይሆን በአብያተ ክርስቲያናቱም አካባቢ እጅግ በተስፋፋበት ዘመን ይህን አዲስ ኪዳናዊ መርሕ (ግዕዝ) በሙሉ ልብ የምንቀበለው እንዴት ነው?

አዲስ ኪዳናዊ ጋብቻ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ጥምረቱ ከባድ የሆነውን ያህል በጥምረቱም ለመዝለቅ ከባድ ፈተና ይጠብቀናል፡፡ የምንከተለው ክርስቶስንና የእርሱን መንገድ ከሆነ፣ ነገሮችን በእርሱ ዐይን መመልከት ይኖርብናል፡፡ መስቀሉ ሁል ጊዜ የሚያመላክተን ወደ ክርስቶስ ነው፡፡ መስቀሉ የዓለምን ፍልስፍና ሳይሆን የክርስቶስን ትምህርት፣ የዓለምን መርሕ ሳይሆን የክርስቶስን ምሳሌ እንድንከተል ነው የሚጠይቀን፡፡ ምክንያቱም ክርስቶስ እንደኖረው እንጂ ዓለም እንደምትለን ለመኖር አልተጠራንም፡፡ ዓለም ትምክህትን ታሳየናለች፤ ክርስቶስ ግን ትሕትናን ያስተምረናል፡፡ እንግዲህ የዓለም መንገድና የክርስቶስ መንገድ ለየቅል ናቸው ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ግጥሚያም ሆነ ምስያ የላቸውም፡፡ ነገሩ እንዲህ ከሆነ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ በዚህ ምድር የኖረው የአገልጋይን/የባርያን መልክ ይዞ በመሆኑ (ፊል 2÷7) እነርሱም የታላቁን መምህር የአገልጋይነት ምሳሌ መከተል ይኖርባቸዋል (ማር 10÷42-45)፡፡ በትዳር ውስጥ የሚገጥሙንን ፈተናዎች መመልከት ያለብን ከዚህ ከደቀ መዝሙርነት ዕይታ አንጻር ሊሆን ይገባል፡፡ ምክንያቱም የደቀ መዝሙርነት ሕይወት የመሥዋዕትነት ሕይወት ነው፡፡ ስለሆነም ጋብቻንም ሆነ ሌሎች ሥነ ምግባራዊ ርእሰ ጉዳዮችን መረዳት ያለብን የመሥዕዋትነት ሕይወት መታወቂያ ምልክቱ ከሆነው ከደቀ መዝሙርነት አንጻር መሆን አለበት፡፡ እንግዲህ መከራን፣ ፈተናንና በደልን ሁሉ ለመሸከም ተጠርተናል ማለት ነው፡፡ መበደል ሊኖር ይችላል፤ መፋታት ግን መፍትሔ አይደለም፡፡ ከልክ ያለፈ መከራ ሊኖር ይችላል፤ ትቶ መሄድ ግን መፍትሔ አይደለም፡፡ መማረር ሊኖር ይችላል፤ ዐይንህን ለዐፈር መባባል ግን መፍትሔ አይደለም፡፡ መስቀሉ የሚያስተምረን ተበድላችሁ ሳለ ይቅር በሉ፤ ተጠልታችሁ ሳለ ውደዱ፤ ተረግማችሁ ሳለ መርቁ፤ ተሰዳችሁ ሳለ ጸልዩ በማለት ነው፡፡ መስቀሉ ለበቀልም ሆነ ለጥላቻ ስፍራ የለውም፡፡ የኢየሱስ ሞት/መስቀል እርሱን መከተል ለሚፈልጉ ሁሉ ምሳሌአቸው ነው፡፡ እናም የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ለመሆን የተጠሩ ሁሉ ራሳቸውን ክደው መስቀሉን ተሸክመው ሊከተሉት ይገባል (ማር 8÷34-35)፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆን ማለት የኢየሱስን መከራ መካፈል፣ የአገልጋይነቱን መልክ መውረስና ዓለም የምትራበውን፣ የምትጠማውንና የምትመኘውን ኀይል መናቅ ነው፡፡ ወንጌላውያኑም ሆኑ የተቀሩት የአዲስ ኪዳን ጸሓፊዎች ደቀ መዝሙርነትን የሚገልጹት መብትን፣ ሀብትን፣ በጥቅሉ እኔነትን ትቶ ክርስቶስን በመስቀሉ መንገድ መከተል በሚለው ትርጕሙ ነው (ማር 10÷17-22)[6]፡፡ በዘዳግም 24÷1 ላይ የምናነበው ሕግ ጋብቻ ከሚያስከፍለው ብርቱ ዋጋ ለማምለጥ ዕድል ይሰጥ ይሆናል፡፡ ኢየሱስ ግን የእርሱን ደቀ መዛሙርት ወደ መጀመሪያው የእግዚአብሔር ፈቃድና ሥርዐት ሲያመላክታቸውና በዚያም መሠረት እንዲኖሩ ጥሪ ሲያቀርብላቸው እንመለከታለን፡፡ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እንዲኖሩ የተጠሩት በሙሴ ሥርዐት ሳይሆን፣ በኢየሱስ ስብከትና ሕይወት በተጀመረው በአዲሱ ሥርዐት ነው፡፡ ስብከቱና ሕይወቱ ለአዲሱ ሥርዐት ሕይወት መርሕ ሆኗል፡፡ ይህም አዲስ ሥርዐተ ሕይወት ቂጣን ማስወገድና አንዱን ጉንጫችንን ሲመቱን ሌላውን ማዞር፣ ሲሰድቡንና ሲያሳድዱን መመረቅ፣ ሲጠሉንና ሲበድሉን መውደድ፣ ወዘተ ነው (ማቴ 5)፡፡ ወንጌላዊው ማቴዎስ "መፋታት አይገባም" ሲለን ይህን አዲሱን ሥርዐተ ሕይወት መሠረት አድርጎ ነው፡፡

[6] Richard B. Hays, *The Moral Vision of the New* Testamen, 364-366.

*በባልና በሚስት መካከል ያለ ግንኙነት የጋራ ጥረትን ይጠይቃል:: መሥዋዕትነቱ ከሁሉቱም ወገኖች ይጠበቃል:: የመሥዋዕትነት ሕይወት ባለበት ስፍራ መፋታት ቦታ የለውም:: ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክቱ ላይ እስከ አሁን ለተባለው ነገር ማሰሪያ የሚሆን ብርቱ ምክር ይሰጠናል፤ “ባሎች ሆይ! ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደደና ራሱን ስለ እርስዋ አሳልፎ እንደ ሰጠ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ”* (ኤፌ 5÷25):: *በዚህ ዐይነት ወደ መጀመሪያው ሥርዐት መመለስና በዚያም መሠረት መኖር ይቻላል:: ምክንያቱም አሁን አንዱ ለሌላው ራሱን አሳልፎ ይሰጣል-ልክ ክርስቶስ እንዳደረገው*[7]::

*አሁን በምንወያይበትን ርእስ ጉዳይ በዚህ ዐይን የምንመለከታቸው ከሆነ፣ መፋታት የሁለት ግለሰቦች ጉዳይ ብቻ ሆኖ አናገኘውም:: ይልቁንም ጉዳዩ የመላውን ኅብረተሰብ ጤናና ምስክርነት ይመለከታል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግለ ሰቦችን በሚጠራበት ጊዜ ዐላማው አንድን ኅብረተሰብ ለመመሥረት ነው:: የኅብረተሰብ ተልእኮ “የዓለም ብርሃን” መሆንና ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው* (ማቴ 5÷14-16):: *ለዚህ መብቃት የሚቻለው ኢየሱስ ባስተማረው የጽድቅ ደረጃ መኖር ስንችል ነው:: መፋታት በሚታሰብበት ጊዜ የኅብረተሰቡም ተልእኮ መታሰብ አለበት:: የኅብረተሰቡን ተልእኮ ያላገናዘበ እርምጃ የኅብረተሰቡን ምስክርነት ያጎድፋል:: ደቀ መዝሙር የጌታን ፈለግ ተከትሎ ይጓዛል እንጂ የራሱን ፈለግ አይቀይስም:: ምክንያቱም የደቀ መዝሙርነት ሕይወት ምን መምሰልና መሆን እንዳለበት የምንማረው ከመስቀሉ ነው:: በመሆኑም ጋብቻ ለኅብረተሰቡ ከሚያስገኘው ጥቅምና ባንጻሩ በኅብረተሰቡ ላይ ከሚያስከትለው ጉዳት አኳያ መታየት ይኖርበታል*[8]:: *በክርስቶስ ስብከትና ሕይወት የተጀመረው አዲሱ ሥርዐት ወይም በመደበኛው አገላለጽ የእግዚአብሔር መንግሥት በርካታ አዳዲስ ገጽታዎች አሉት:: አሁን እኛ የምንኖረው በሁለት ተጣራሽ ዘመኖች መካከል ነው-በአሁኑ አሮጌው ዘመንና በመጻኢው አዲሱ ዘመን:: መጻኢው አዲሱ ዘመን በርግጥ መጥቶአል:: የዚህ መጻኢ ዘመን አንዱ ገጽታ በአዲስ ሕይወትና በአዲስ መንፈስ መመለስ ነው:: ጌታ ኢየሱስ የሙሴን ሕግና ሥርዐት አልፎ “ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም”* (ማቴ 19÷8) *ሲለን፣ አሁን ሁሉም ነገር በእርሱ “አዲስ ፍጥረት” መሆኑን እያሳሰበን ነው:: የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አዲስ ፍጥረት ናቸው:: በመሆኑም እነርሱ አሁን መኖር ያለባቸው “ከጥንት በነበረው ሥርዐት” መሠረት ነው:: “በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም”* (ማቴ 5÷14-16):: *ከሰዎች ዕይታ ሊሰወር በማይችል ኅብረተሰብ መካከል መፋታት ስፍራ የለውም:: እንግዲህ መፋታት የተጠላ ተግባር የሆነው የአዲሱ ፍጥረት ምልክት ስላልሆነ ነው:: የአዲሱ ፍጥረት ምልክት “አንድ ሥጋ ይሆናሉ” በሚለው ጋብቻዊ ጥምረት በታማኝነት ጸንቶ መኖር ነው:: በመጨረሻም በራእየ ዮሐንስ ውስጥ እንደምናነበው፣ የበጉ ሰርግ፣ ምድራዊ ጋብቻዎች ሁሉ ተፍጻሜታቸውን የሚያገኙበት ሆኖ እናገኘዋለን:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ የምናየው ጋብቻ ወደ ታላቁ ሰርግ የሚያመላክት ከሆነ፣ መፋታት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አይገጥምም ማለት ነው*[9]:: *ቅዱሳት መጻሕፍት በተለይ ሐዲስ ኪዳን በጋብቻና በፍቺ ላይ የሚሰጠን ትምህርት ፍጹም ወጥነት ያለው ነው:: ይኸውም ጋብቻ አንድ ለአንድ እና ቋሚ ነው:: ደግሞም ክርስቲያኖች ጋብቻቸውን እንዲመለከቱት የተጠሩት የደቀ መዝሙርነት መገለጫ አድርገው ነው::*

[7] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 364 - 366::
[8] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 364 - 366::
[9] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 364 - 366::

ክርስቲያኖች መፋታትን መጥላት አለባቸው። ምክንያቱም መስቀሉን ተሸክመው እንዲኖሩ ተጠርተዋልና[10]።

# III. የዶክተር ወዳጄነህ መሐረነ እና የመጋቢ ሙሉጌታ ግዛት የሙግት አካሄድ

## 1. የዶክተር ወዳጄነህ ሙግት

ዶ/ር ወዳጄነህ ፍቺው ትክክል መሆኑን የሞገቱት በዚህ መልክ ነው፦

1. የወ/ሮ አስቴር የቀድሞ ባል፣ ፕሬዝዴንት ሳሙኤል ዶ በአሠቃቂ ሁኔታ ተገድሏል።
2. ጋብቻውን ያካሄድሁት ጌታን በተቀበልሁ በአምስት ወር ውስጥ ነው።
    - "ጌታን ባገኘሁ በአምስት ወሩ ከአስቴር ጋር ተዋወቅን...የደኅንነት ትምህርት እየተማርኩ ነበረ"
3. ከወ/ሮ አስቴር ዐይን የሚወጣው ኀይል ያስጨንቀኛል።
    - "ትኩር ብላ ስትመለከት ከዐይኗ የሚወጣው ኀይል ግን ያስጨንቀኝ ነበር"
4. ለጋብቻ የጠየቀችኝ እርሷ ናት።
    - "እኔ አሁን በምነግርህ ላይ አንድ ሐሰት ብጨምርበት እግዚአብሔር ምሕረት አያድርግልኝ። ለጋብቻ የጠየቀችኝ እርሷ ናት። እኔ እጅግ ተቸገርሁ"
5. "አስቴር ከእኔ በዕድሜ በ15 ዓመት ትበልጣለች"።
6. አስቴር፣ "ከሁለት የተለያዩ ወንዶች ሁለት ልጆች አሏት"።
7. አስቴር ከመናፍስቱ ዓለም ጋር ጥብቅ ቊርኝት ከነበረው ሰው ጋር በጋብቻ አብራ ኖራለች፣ ይህ ደግሞ እርሷም ከመናፍስት አሠራር ውስጥ መቆየቷን የሚያሳይ ነው።
8. የወይዘሮ አስቴር ሀብት የተገኘው ከቀድሞ ባለቤቷ ሳሙኤል ዶ ሲሆን፣ ሳሙኤል ዶ ደግሞ ይህን ንብረት ያገኙት ከላይቤሪያ ሕዝብ ዘርፈው ነው።
9. ከስድስት ወር የጋብቻ ጊዜ በኋላ ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ጥሪ ደረሰኝ።
10. ስለዚህ ፍቺ መፈጸሜ ቃለ እግዚአብሔርን እንደ ሚጻረር እኩይ ተግባር መታየት የለበትም። እንዲያውም እግዚአብሔር እንድፈታ ተናግሮኝ የወሰድሁት እርምጃ ብቻ ሳይሆን፣ ወይዘሮ አስቴር በካሪዝማ መጽሔት ላይ ባወራችብኝ አሉባልታ ታርጃለሁ በመታረዴም ትልቅ የአገሪቱን ማኅተም እንድፈታ ሹመት ከአምላክ ዘንድ ተቀብያለሁ።

## 2. የመጋቢ ሙሉጌታ ግዛት ሙግት

የዶ/ር ወዳጄነህ የጥምቀት ትምህርት መምህርና መንፈሳዊ አባት የዶ/ር ወዳጄነህን የፍቺ አካሄድ ትክክለኛ መሆኑን ያስረዱት የሚከተለውን የሙግት አካሄድ በመከተል ነው፦

1. "'ንብረት የመካፈል መብት አለኝ' ብሏል ማለት አሉባልታ ከመሆን አያልፍም"
2. የወይዘሮ አስቴር የቀድሞ ባል የሆኑት ሳሙኤል ዶ ባዕድ አምልኮ የሚያካሂዱ፣ የንጹሓን ሰዎች ደም ያለባቸውና በመንፈስ አሠራር ውስጥ የነበሩ ሰው ናቸው።

---

[10] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 364 - 366።

- "ጌታ በልቤ ያመጣ የነበረው...ሳሙኤል ዶ መሪነቱ በደም የሰከረ በተጨማሪ በመናፍስቱ ዓለም ይንቀሳቀስ የነበረ ሰው መሆኑን ነበር"

3. "ከሳሙኤል ዶ ጋር በሚስትነት የነበረችና ልጅ የወለደችለት የሚለው ጉዳይ በእርግጥም በዶ/ር ወዳጄነህ ፊት ጠላት መሰናክል እንዳስቀመጠ እርግጠኛ ሆንሁ"
4. "የደም እጅ ያለበት ሰው ጋር የኖረች ሴት ጋር መኖር ማሰብ...በጭራሽ የሚታሰብ አይደለም"፡፡
5. "በጌታ ፊት ወድቄ አጥብቄ መጸለይ ጀመርሁ" እግዚአብሔርም አስቴር ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር ትስስር ያላት ሴት እንዲሁም ያልተረጋጋች ሴት መሆኗን እግዚአብሔር ተናገረኝ፡፡ ለዚህም ምስክሩ (1) "ዐይኗ አንድ ስፍራ አይረግጥም" (2) "አካባቢዋን በጥርጣሪና በፍርሓት ትመለከታለች" (3) "መንፈስ ቅዱስ ውስጧን ሲፈትሸው ነፍሷ አላረፈም" (4) "ጌታ በልቤ ቃል ያቀብለኝ ነበር" (5) "ነገሮችን እመለከት የነበረው ከመንፈሳዊ አካሄድ ጋር" ነው፡፡ (6) "ዛሬ ጌታ የገለጠልኝን የጠላት አሠራር ምስጢር...ወደ ፊትም ቢሆን ጌታ ጸጋውን ባበዛልኝ መጠን ከመናፍስቱ ዓለም ጋር በመዋጋት ነፍሳትን ለማዳን ቊርጠኛ ዐላማዬ ነው" (7) "ፍጹሞ ይህን ግንኙነት እንድቃወም መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ቊጣ ሞላ"፡፡
6. ጠላት ነፍስ ለማጥፋት ሲል ሆነ ብሎ ያዘጋጀው ትዳር ነው
7. ፍቺውን ያካሄደው ራሱ እግዚአብሔር ልዩ በሆነ አሠራሩ ነው፡፡ (1) "ከረቂቅ የጠላት አሠራር ጌታ አስመልጦት ታላቅ ሥራ መሥራቱ በዚህ መልክ መጨረሱም እግዚአብሔር ለዐላማው ተጠቅሞበታል ባይ ነኝ" (2) "ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ መናገር እውዳለሁ...ይህ የዶ/ር ወዳጄነህ መሐረነ የሕይወት ተሞክር እግዚአብሔር በተለየ መንገድ በግል ሕይወቱ ያደረገው መለኮታዊ አሠራር" ነው፡፡
8. ወጣቶች ይህን እግዚብሔር በልዩ አሠራሩ ያስሄደውን መንገድ ከመከተል ይልቅ ቅራኔን በማብረድ በሰላም መኖር ይጠበቅባቸዋል፡፡
9. ዶክተር ወዳጄነህ የእግዚአብሔር ትልቅ ዐላማ ያለብት የእግዚአብሔር ሰው ነው፡፡
10. ስለዚህ ፍቺው በመለኮታዊ አሠራር የተካሄደ ትክክለኛ እርምጃ ስለሆነ ፍቺውን ማውገዝ ስሕተት ነው፡፡

መጋቢ ሙሉጌታን፣ ዶ/ር ወዳጄነህ፣ "'ንብረት የመካፈል መብት አለኝ' ብሏል ማለት አሉባልታ ከመሆን አያልፍም" ወደሚለው ድምዳሜ ያደረሳቸው ጉዳይ ምን እንደ ሆነ ገልጸዋል፤ ይኸውም፣ "የዶ/ር ወዳጄነህ ጨዋታና የበሰለ ንግግሩ በነፍስህ ውስጥ ተጽእኖ የሚያሳድር፣ ግብዝነት የማይታይበት...ብሩኅ አእምሮ ያለው" የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በርግጥ ግለሰቡ የንባብ ሰው፣ የብሩኅ አእምሮ ባለቤትና ጨዋታ ዐዋቂ ሰው መሆናቸው "'ንብረት የመካፈል መብት አለኝ' ብሏል ማለት አሉባልታ ከመሆን አያልፍም" ወደሚለው ድምዳሜ ያደርሳልን? "የተማሩና ጨዋታ ዐዋቂ" የሆኑ ሰዎች የሰውን ገንዘብ ሊመኙ አይችሉም ብሎ መደምደም ትክክለኛ የሆነ የሙግት አካሄድ ነውን? ለዐሥራ አንድ ዓመት የተለዩትን ምናልባትም በቴሌፎንና በደብዳቤ ብቻ ለሚያቁት ሰው እንዲህ ዐይነቱን ምስክርነት መስጠትስ ፍርዳቸውን ሚዛናዊ ያደርገዋል (ዶ/ር ወዳጄነህ ባለፉት ዐሥራ ሁለት ዓመታት በኢትዮጵያና በአሜሪካን አገር የቆዩ ሲሆን፣ መጋቢ ሙሉጌታ ደግሞ ከዐሥር ዓመት በላይ በሲውዘርላንድ መኖራቸውን ልብ ይሏል)? የሰው ልጆች በሰዓታት ውስጥ የጠባይ ለውጥ ሊያመጡ በሚችሉበት ሁኔታ ማስረጃን ሳያገናዝቡ እንዲህ ዐይነት ብያኔ መስጠት በተለይ ከአንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ይጠበቃልን?

መጋቢ ሙሉጌታ ግዛት ፍቺው በእግዚአብሔር በመለኮታዊ አሠራ የተካሄደ ጉዳይ መሆኑን ከዚህም የተነሣ ፍቺውን ማውገዝ ትክክል እንዳይደለ ለማሳየት ጥረት ያደረጉ ቢሆንም፣ አስገራሚው ጉዳይ መጋቢ ሙሉጌታ ፍቺውን ለማጽደቅ ያቀረቧቸው የሙግት ነጥቦች፣ ድምዳሜያቸውን በጭራሽ የሚደግፍ ዐቅም የሌላቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ ለድምዳሜው አንዳችም ጠቀሜታ የሌላቸው እንዲያውም የተውገረገሩና እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ነጥቦችን ጽፈዋል። መጋቢ ሙሉጌታ በጽሑፋቸው ውስጥ፣ "ሳሙኤል ዶን ለሥልጣን ካበቁት በክፉ መንፈስ ከሚንቀሳቀሱ ጄኔራሎች መካከል አንዱ የነበረው ጄኔራል ቡት ናክድ (General Butt Naked) ወደ ጌታ ሲመጣ ስሙ መጋቢ ኢየሱ ሚሊቶ ብለይ (Pastor Joshua Milton Blayee) ተብሏል" ብለውናል። እንግዲያው ይህ ሰው ከሳሙኤል ዶ ጋር "በመናፍስት አሠራር ውስጥም ሆነ ንጹሕ ደም በማፍሰስ ውስጥ" የነበረ ሰው ሆኖ ሳለ፣ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ ከተቀበለ በኋላ፣ በእግዚአብሔር ምሕረትና ትድግና የጌታ አገልጋይ ያውም መጋቢ መሆን ከቻለ፣ ወ/ሮ አስቴር ይህን ዕድል በማግኘት ከመናፍስ አሠራር ሊወጡ አይችሉም የተባሉበት ምክንያት ምንድን ነው (ወ/ሮ አስቴር በመናፍስቱ አሠራር ውስጥ ነበሩ ብንል እንኳ ማለቴ ነው)? አንድን ክርስቲያን ሴት ጥንት በመናፍስት "አሠራር ውስጥ ስለነበርሽ"፣ "ለትልቅ አገልጋይ" ሚስት ልትሆኚ ስለማትቺዪ ባልሽ ሊፈታሽ ይገባል ብሎ መበየን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን?

## IV. የሚከተሉት ጉዳዮች ለሙግቱ ፍሰት አንዳችም እርባና የላቸውም

ዶ/ር ወዳጄነህ ከጌሜም መጽሔት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ሰፊ ቦታ በመስጠት ሐተታ የቀረቡባቸው የሚከተሉት ነጥቦች ቢሆኑም፣ እነዚህ ጉዳዮች ፍቺውን ማካሄዳቸው ተገቢ ነበር ወይስ አልነበረም ለሚለው የሙግት ድምዳሜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አንዳችም ጠቀሜታ እንደሌላቸው አንባብያን በውል ሊያስተውሉት ይገባል:—

1. አግባኝ የሚለውን ጥያቄ ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረቡት ወ/ሮ አስቴር መሆናቸው [ይህ የዶ/ር ወዳጄነህ ንግግር ትክክል ነው ብለን እንኳ ብንቀበል፣ ግለሰቡ በወ/ሮ አስቴር መወደዳቸውን እንጂ ፍቺው ትክክል ነበር ወይስ አልነበረም ለሚለው ጉዳይ አንዳችም ጠቀሜታ የሌለውም። ይህ እንዳለ ሆኖ የሚከተሉት መረጃዎች ግን ያጋብቻውን ጥያቄ ያቀረቡት ዶ/ር ወዳጄነህ ራሳቸው ለመሆናቸው ፍንጭ ተቋሚ የሆኑ ጉዳዮች በወ/ሮ አስቴር ጽሑፍ ላይ ማስተዋል ይቻላል። ይኸውም:— (1) ዶ/ር ወዳጄነህ የጋብቻውን ጥያቄ ያቀረቡት በእማኝ (በዶ/ር መከተ) ፊት መሆኑ፣ (2) ወ/ሮ አስቴር የጋብቻውን ጥያቄ ለመቀበል የሚያስቸግራቸው ከሌላ ሰው የወለዱት አንድ ልጅ እንዳለ በገለጹበት ወቅት ዶ/ር መከተ፣ ዶ/ር ወዳጄነህም ከሌላ ሴት የወለደው ልጅ እንዳለውና ይህም ተመሳሳይ ሁኔታ ስለሚያጋራቸው ጋብቻውን እንዳማያሰናክል መገለጹ፣ (3) "በርግጥ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሽኝ ሚስቴ ነሽ ይህንን መቀበል አለብሽ። እኔ እግዚአብሔርን ታምኜ የምኖር ሰው ነኝ፤ ምንም ጥርጣሬ አይደርብሽ። ከእኔ ጋር በሚኖረን የትዳር ጊዜ በጣም ነው የምንከባከብሽ፤

እንደ ሰበባ እያበብሽ ነው የምትኖሪው" የሚለው የዶ/ር ወዳጄነህ ንግግር[11]፣ ጥያቄውን ማቅረባቸውን የሚያመለክት ነው:: (4) እንደ አገሪቱ ባህል ዶ/ር ወዳጄነህ ራሳቸው ሽማግሌ ወ/ሮ አስቴር ቤት መላካቸው:: (5) ዶ/ር ወዳጄነህ የሚከተለውን ንግግር በአክስታቸው ልጅ ፊት ማለታቸው፣ "አስቱ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዶክተር መከተ ጋር ሆኜ አዲስ አበባ ራስ ሆቴል ቁጭ ብለን ነበር አይደለ የጋብቻ ጥያቄ ያደረኩልሽ? ዛሬ ደግሞ እዚህ ሂልተን ሆቴል እናፈርሰዋለን" የሚለው ጉዳይ "አግባኝ" የሚለውን ጥያቄ ወ/ሮ አስቴር እንዳላቀረቡ የሚያሳይ ነው::

2. የወ/ሮ አስቴር የቀድሞ ባል የነበሩት የቀድሞው የላይቤሪያ ፕሬዝደንት ሳሙኤል ዶ የሞቱት "በአውሮፕላን አደጋ ነው ወይስ በሰው ተገድለው" የሚለው ጉዳይ ዶ/ር ወዳጄነህ ፍቺውን ከማካሄዳቸው ጋር አንዳችም ግንኙነት የለውም::
3. እንደ ዶ/ር ወዳጄነህ "ጌታን ጋገኑ" ከአምስት ወር በኋላ ከሆነ፣ ጋብቻውን መፈጸማቸውን ነግረውናል:: በዚሁ ዘገባቸው ውስጥ ጋብቻውን የፈጸሙት ከውሃ ጥምቀት በኋላ እንደ ሆነ እንዲሁም ብዙ ይጸልዩ ስለነበር መንፈሳዊ ሕይወታቸው በአስደናቂ ሁኔታ እንደ ዐደገ ገልጸውልናል:: ይህ በሆነበት ሁኔታ ለጋብቻ የማልበቃ መንፈሳዊ ለጋ ነኝ ማለታቸው ብዙ አሳማኝነት የለውም::
4. ከወ/ሮ አስቴር ዐይን የሚወጣው ኀይል ዶ/ር ወዳጄነህን ማስጨነቁ በግለሰቡ መንፈሳዊነት ላይ ትልቅ ጥያቄ የሚያሳድር እንጂ ፍቺውን የሚደግፍ ጉዳይ አይደለም:: የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት፣ ደግም ልደት ያገኘ ሰው፣ ከሌላው ሰው ዐይን የሚወጣው ኀይል እንዴት ያስጨንቀኛል ሊል ይችላል? "በእኛ ያለው ከዓለም ካለው ይበልጣል" የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ፣ ቢሆን ቢሆን ከዶ/ር ወዳጄነህ "ዐይን የሚወጣው ኀይል" ነበር ወ/ሮ አስቴርን ማስጨነቅ እንጂ እርሳቸው በጭራሽ መጨነቅ አልነበረባቸውም:: "ከአፍሪካ መናፍስት ጋር የመታገል" ብቃት እንዳላቸው ገልጸውልን በአንዲት ግለሰብ ሴት ዐይን መታወካቸው አስገራሚ ነው:: የሆነ ሆኖ፣ ይህ ጉዳይ ፍቺው ትክክል ነበር ወይስ አልነበረም ለሚለው ጉዳይ አንዳችም ፋይዳ የሌለው ሲሆን፣ ግለሰቡ ግን ርእስ ጉዳዩን እጅግ ውስብስብ እንዲሁም ጥልቅ መንፈሳዊ ይዘት በማላበስ ፍቺውን ለማጽደቅ ትልቅ ሙከራ አድርገዋል::
5. ወ/ሮ አስቴር ሁለት ከተለያዩ ባሎች ሁለት ልጆች መውለዳቸው እሙን ቢሆንም፣ ዶ/ር ወዳጄነህም "በዓለም ሳሉ" የወለዷት ሴት ልጅ እንዳለቻቸው መስክረዋል:: ከጋብቻው በፊት የተወለዱት የልጆች ብዛት ፍቺው የእግዚብሔር ሐሳብ ያለበት ነው ወደሚለው ድምዳሜ ለማድረስ ይቅርና ከድምዳሜው ጋር አንዳችም ታያያዥነት የሌለው ነው::
6. ፕሬዝደንት ሳሙኤል ዶ ባዕድ አምልኮ ልምምድ ነበራቸው የሚለውም ጉዳይ ፍቺውን ለማጽደቅ አንዳችም ጠቀሜታ የለውም:: እኝህ ሰው የባዕድ አምልኮ ልምምድ ነበራቸው ማለት ባለቤታቸውም በልምምዱ ውስጥ ተሳታፊ ነበሩ የሚለውን ጉዳይ ተሳቢ የሚያደርግ አይደለም (ለመሳተፋቸው ተጨባጭ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ):: "ባል ባለበት ስፍራ ሁሉ ሚስትም አትጠፋም" ቢባል እንኳ፣ ወ/ሮ አስቴር እንደ አንዳንድ ክርስቲያኖች ከባዕድ አምልኮ ወደ ክርስትና መምጣታቸውን የሚያመለክት እንጂ[12]፣ ዶ/ር ወዳጄነህ ፍቺውን

[11] ዶ/ር ወዳጄነህ ይህን መሰሉን በርካታ ንግግር እንዲያውም አንቺን ከምተው ክርስቶስን ብተው ይቀለኛል ያሉበትን ደብዳቤ ከዚህ መጽሔት አዘጋጅ እጅ ማግኘት እንደሚቻል ተገልጾልኛል::

[12] በዚሁ ዶ/ር ወዳጄነህ ቃለ ምልልስ ባደረጉበት መጽሔት ላይ የአንድ ክርስቲያን ወንድም የቀድሞ ከመናፍስቱ ዓለም ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንደ ነበረው ምስክርነት መስጠቱን ያስቷውሷል:: በቅዱሳት መጻሕፍት ከዚህ ዐይነቱ ልምምድ በክርስቶስ የተጠሩትን ሰዎች በስፋት እናነባለን::

ለማፍረስ መሠረት ሊሆናቸው በጭራሽ አይችልም። ብዙዎቻችንን ክርስቶስ የጠራን ጥሩ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ በነበርንበት ወቅት ነው። እኛ ከቈሻሻ ስፍራ መጠራታችን የክርስቶስን ሁሉን ቻይነትና ታላቅ ፍቅር አመልካች እንጂ፣ የፍቺ መሠረት አይደለም፤ ሊሆንም አይገባውም።

፯. ፕሬዝደንት ሳሙኤል ዶ በአግቃቂ መንገድ መገደላቸው ከፍቺው ጋር አንዳችም ግንኙነት የለውም። ዶ/ር ወዳጄነህም ሆኑ መንፈሳዊ መምህራቸው መጋቢ ሙሉጌታ በሳሙኤል ዶ አግቃቂ አሟሟት ላይ በፎቶ ግራፍ የተደገፈ ሰፊ ዘገባ አቅርበዋል። ይህ ዘገባ ግለሰቡ መፈንቅለ መንግሥት (ኩ ዴታ) በተካሄደባቸው ወቅት የተፈጸመባቸውን ግፍ አመላካች እንጂ፣ በፍቺው ርእሰ ጉዳይ ላይ አንዳም ጠቀሜታ የለውም። ምናልባት ዶ/ር ወዳጄነህና መጋቢ ሙሉጌታ ይህን ጉዳይ አድምቀው የነገሩን ሀሳባችንን ከዋናው ቍም ነገር ለመቀልበስ አስበው አልያም ነገሩን ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ይዘት ለማላበስ ፈልገው ይመስላል። ይህ የሙግት ነጥብ ከድምዳሜው ጋር እንዳችም ተያያዥነት የሌለው መሆኑን ግን አንባብያን ሊስቱት አይገባም። በፕሬዝደንት ሳሙኤል ዶ ላይ የቀረበው ሰፊ ዘገባ ተዛማጅነት በሌለው መንገድ ወ/ሮ አስቴርን ጥላሸት የሚቀባ ብቻ ሳይሆን፣ የወ/ሮ አስቴር የአብራክ ክፋይ የሆነውን የሳሙኤል ዶን ልጅ ልብ የሚያደማ ነው።

፰. ወ/ሮ አስቴር የተንጣለለ ቤት፣ ያማረ መኪና እንዲሁም እጅግ ብዙ ሀብት ባለቤት መሆናቸው ከፍቺው ርእሰ ጉዳይ ጋር ቅንጣት ታህል ግንኙነት የለውም። ሳሙኤል ዶ ሀብታቸውን ያከማቹት ዘርፈው ነው ወይስ ሠርተው የሚለው ጉዳይ የዶ/ር ወዳጄነህ ኀላፊነት አይደለም። ዘርፈው ለመሆኑም አንዳችም መረጃ አላቀረቡም። ሳሙኤል ዶ ሀብቱን ያከማቹት እንደ ተባለው በዝርፊያ ቢሆን፣ በእሳቸው ኀጢአት ባለቤታቸውን መኰነን እንኳን ሐዲስ ኪዳን ብሉይም የሚደግፈው አይደለም (ያውም ጌታን ከማወቃቸው በፊት ያደረጉትን ግፍ)። ዶ/ር ወዳጄነህ፣ "አስቴር የገዛችልኝን ልብስ አቃጠልሁት" እንዲሁም መጋቢ ሙሉጌታ ግዛት፣ "ጌታ መንፈስ ቅዱስ በአንድ ጉዳይ እንድጸልይ ስላሳሰበኝ፣ ላይቤሪያ እያለሽ ድግምት የተደረገባቸው ጌጣጌጦች እንዳሉሽ ጌታ ይናገረኛል አምጥተሽ ልጸልይበት አልኳት" የሚለው ጉዳይ ምን ዐይነት ባዕድ አምልኮ እንደ ሆነ እኔ በግሌ አልገባኝም። በተለይ መጋቢ ሙሉጌታ ነገረ መለኮትን በኮሌጅ ደረጃ የተማሩ ሰው ሆነው ሳለ፣ ይህ ዐይነቱን በዕድ ልምምድ "ጌታ መንፈስ ቅዱስ ተናገረኝ" ማለታቸው አስደንቆኛል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ ጌታን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን ከመቀበላችን የተነሣ፣ በእኛ ላይ የተጋሄዱ መናፍስታዊ አሠራሮች ሁሉ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ድል እንደሚነሡ እንጂ፣ "ድግምት አፍራሽ ባለመገለጥ" ዘንድ ቍሳቍሶችን ተሸክመን በመሄድ፣ ድግምት እናስፈርሳለን የሚለው ጉዳይ፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ የሌላ ሃይማኖት ትምህርት ካልሆነ በቀር፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አይደለም—በሊቃውንቱም ዘንድ ሆነ በመጽሐፉ የለም!!!

፱. ዶ/ር ወዳጄነህ የእግዚአብሔርን ስም እየጠሩ ጋብቻው በተፈጸመበት ወቅት ወ/ሮ አስቴር ዓለማዊ መሆናቸውን መግለጻቸው ፍቺ ማካሄዳቸውን ሠናይ ምግባር አያደርግላቸውም። ክርስቲያን ዓለማዊ ማግባት እንደሌለበት የሚናገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማንኛውም ሰው አንብቦ የሚረዳው እውነት ቢሆንም፣ ክርስቲያን በተለያየ ምክንያት ዓለማዊ ቢያገባ ያገባትን ሴት ይፍታ የሚል የነገረ መለኮት ትምህርት ታይቶም ሆነ ተሰምቶ አይታወቅም። መጽሐፍ አንድ ክርስቲያን ዓለማዊ ከሆነች ሴት ጋር የገብረ ሥጋ ግንኙነት ቢያድርግ ግለሰቡ ከዓለማዊቷ ሴት ጋር አንድ አካል እንደ ሆነ በግልጽ ማስተማሩን ልብ

ይሏል። "ጋብቻ ቅዱስ" ነው የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አማንያንም ሆኑ ኢአማንያን የሚያካሂዱት ጋብቻ ክቡር መሆኑን እንደሚያመለክት ልብ ይሏል። እንዲያውም፣ "ያላመነው ወገን ባመነው ሰው የተቀደሰ ነው" (1ቆሮንቶስ 7) የሚለው መለኮታዊ ቃል ያላመነው ሰው ያመነውን ወገን ምስክርነትና ሕይወት በመመልከት ወደ ክርስቶስ የመምጣት ዕድል እንዳለው የሚያሳይ እንጂ፣ ለፍቺ ምክንያት እንደማይሆን አስረጅ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ወ/ሮ አስቴር ጋብቻውን በሚያካሂዱበት ወቅት ክርስቲያን እንደ ነበሩ የሚያመለክቱ በርካታ ጠቋሚ ሐሳቦችን ከጽሑፋቸው ላይ ማስተዋል ይቻላል። ይኸውም፡— (1) ሁለቱም ወገኖች ጋብቻውን ከማካሄዳቸው በፊት እማኞች ባሉበት (ለምሳሌ ዶ/ር መከተ) ስለጋብቻው ዘወትር ጸሎት ማድረጋቸው። (2) ወ/ሮ አስቴር ይነገራቸው የነበረው "መገለጥ" ምናልባት እውነት ሳይሆን ቀርቶ፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልወጣ የሚለው ፍርሓታቸውና ዶ/ር መከተ በተደጋጋሚነት የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳለበት መግለጻቸው። (2) ዶ/ር መከተና ዶ/ር ወዳጄነህ ጎተራ ሙሉ ወንጌል ከሰሙት መልእክት ጋር ተመሳሳይ የሆነ መልእክት ሰማን ብለው ለወ/ሮ አስቴር መንገራቸው። (3) ዶ/ር መከተና ዶ/ር ወዳጄነህ ከሥራ በኋላ ለተከታታይ ጊዜያት ጸሎት መጸለያቸው። (4) ወ/ሮ አስቴር ጋብቻውን ለማካሄድ የሚያስችላቸውን የሕይወት ምስክርነት ከቤተ ክርስቲያናቸው ዋና መጋቢ የተጻፈ ደብዳቤ ይዘው መምጣታቸው። ዶ/ር ወዳጄነህ አስቴር በ8ቀን ውስጥ ከቤተ ክርስቲያን አባል መሆኗን የሚገልጽ ደብዳቤ አመጣች ይላሉ? መጋቢ አንፍሬ ዓሊጋዝ ምን ነክቷቸው ነው የ8ቀን ክርስቲያንን "አባላችን ነች" ብለው ደብዳቤ የሚሰጡት። በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በስፋት የመሠራበት ጉዳይ አንድ ሰው የጥምቀት አልያም የእምነት ማጽኛ ትምህርት ቢያንስ ለአምስት ወር ከተከታተለና የውሃ ጥምቀት ከወሰደ በኋላ ነው የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል የሚሆነው። (5) ከጎተራው ጸሎትና መልእክት በኋላ ወ/ሮ አስቴር "ጌታ ተናገረን" ማለታቸውን ዶ/ር ወዳጄነህ ገልጸውልናል። ነገር ግን አንድ ዓለማዊ ሴት "ጌታ ተናገረን" ይላልን? ትንቢቱን ያመጣው ግለሰብ ትንቢቱን "እንዲት እኅት" ብሎ መናገሩ የወ/ሮ አስቴርን ክርስቲያን የሆኑ "እኅት" መሆናቸውን አያሳይምን?

10. ዶ/ር ወዳጄነህ ፍቺውን ያካሄድሁት ከዐሥራ ሁለት ዓመት በፊት ስለሆነ፣ በጉዳዩ ላይ አስተያየት መጠየቁ ትክክል አይደለም እንዲሁም ወ/ሮ አስቴር በካሪዝማ መጽሔት ላይ ቃለ መጠይቅ ማድረጓ ስሕተት ነው ማለታቸው ትክክል አይደለም። የጌታ ደም እንጂ የጊዜ ርዝመት ኀጢአትን አያጸዳምና። ወ/ሮ አስቴር በቅርቡ ይህን ጉዳይ በካሪዝማ መጽሔት ላይ ይፋ ማድረጋቸው ዶ/ር መከተ ለወ/ሮ አስቴር "እግዚአብሔርን ጠብቂ ጌታ የማታ ማታ ሊያሸንፈው ይችላል" ማለታቸውን መሠረት ያደረገ እንዲሁም ወ/ሮ አስቴር ከብዙ ዓመት በኋላ የተካሄዱ ፍቺዎች በእግዚአብሔር ርዳታ ዳግም አንድ የመሆናቸውን ምስክርነት መስማታቸው ወ/ሮ አስቴር ጌታን እየጠበቁ መቆያታቸውን የሚያሳይ ነው።
11. ዶ/ር ወዳጄነህ ፍቺውን ከፈጸሙ በኋላ ለበርካታ ዓመታት በአገልግሎት የመቆየታቸው ጉዳይ፣ የቤተ ክርስቲያንን ድካም የሚያሳይ እንጂ ድርጊታቸውን የሚያጸድቅ አይደለም።
12. ዶ/ር ወዳጄነህ ወ/ሮ አስቴር በዕድሜ እንደሚበልጧቸው ተናግረዋል፤ ከቀረቡት መረጃዎች ተነሥተን እንኳ የዕድሜውን ጉዳይ ብናሰላ፣ ነገሩ እጅግ አወዛጋቢ ሆኖ እናገኘዋለን። የሆኖ ሆኖ ይህ ጉዳይ ዶ/ር ወዳጄነህ ፍቺውን እንዲያካሂዱ የይለፍ ፈቃድ የሚሰጣቸው አይደለም። ዶ/ር ወዳጄነህ ከአሁኗ ሚስታቸው ከዘማሪ ሶፊያ ከ15 ዓመት በላይ

እንደሚበልጡ የአደባባይ ምስጢር ነው:: ወንድ ልጅ ከሴት ልጅ በዕድሜ መብለጥ አለበት አለበለዚያ ጋብቻውን ማፍረስ አለበት የሚለው ሕግ ከየት የተቀዳ ነው?

በአጠቃላይ ዶ/ር ወዳጄነህ ከጉዳዩ ጋር አንዳችም ተያያዥነት የሌላቸውን በርካታ ጉዳዮች ማቅረባቸው፣ "የወ/ሮ አስቴርን ስም በማጉደፍ ፍቺውን ለማጽደቅ ልሞክር" የሚለውን ርካሽ ቴክኒክ የሚያጋልጥ እንጂ ለርእሰ ጉዳዩ አንዳችም ፋይዳ የለውም:: አስገራሚው ጉዳይ ወ/ሮ አስቴር በቃለ ምልልሳቸው ወቅት ከዐሥራ አምስት በላይ የሆኑ ትልልቅ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን በስም በመጥቀስ እንዲሁም በርካታ የጽሑፍ መረጃዎችን በማቅረብ ቃለ መጠይቁን ማካሄዳቸውን አንባብያን ልብ ሊሉት የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል:: ዶ/ር ወዳጄነህ ግን ወ/ሮ አስቴር የጠቀሱትን ጥቂት ግለሰቦች በስም በመጥራት፣ "መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸው ናቸው" ከማለት ባለፈ ድርጊቱ ትክክል ነበር ወይስ ትክክል አልነበረም የሚለውን ጉዳይ አልተናገሩም:: ሰዎቹን ማንቈለጳጰስ ከሙግቱ ፍሰት ጋር አንዳችም ተያያዥነት የለውም:: ምናልባት ተማርሁት የሚሉት የሥነ ልቡና ትምህርት፣ ይህ ዐይነቱ ጅምላስቲክ አዋጪ ነው ብሏቸው ይሆናል::

በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ዶ/ር ወዳጄነህ እኔ ፍቺውን ለመፈጸም የመጀመሪያውን እርምጃ አልወሰድሁም ለማለት ሙከራ አድርገዋል:: ይህ ግን ፍጹም ስሕተት ለመሆኑ የተወሰኑ ማስረጃዎችን እንመልከት:: (1) "ከአንቺ ጋር አልኖርም" ብለው ሻንጣቸውን ጠቅልለው ከቤት የወጡት ዶ/ር ወዳጄነህ ናቸው:: (2) "እግዚአብሔር ተለይ ብሎኛል" እያሉ ያሉት ወ/ሮ አስቴር ሳይሆኑ ዶ/ር ወዳጄነህ ናቸው:: (3) "በኀጢአት በተገኘ በተንግለለ ቤት ውስጥ አልኖርም" ያሉት ዶ/ር ወዳጄነህ ናቸው:: (4) የዶ/ር ወዳጄነህ መንፈሳዊ መምህር ፍቺው እግዚአብሔር በልዩ አሠራሩ ያከናወነው ድርጊት ነው ማለታቸው ፍቺውን መንፈሳዊ ልጆቸው የሆኑት ዶ/ር ወዳጄነህ እንዳካሄዱት ታሳቢ ያደረገ ነው:: (5) ዶ/ር ወዳጄነህ በሐሰት ባለቤቴ ጠፍታለች በማለት በሐሰት አስመስክረው ዳግም ጋብቻ ያካሄዱት ዶ/ር ወዳጄነህ ናቸው (ይህን ሰነድ ማግኘትም ሆነ ማየት የሚፈልጉ ከዚህ መጽሔት አዘጋጅ ዘንድ ማግኘት ይችላሉ):: (6) ወ/ሮ አስቴር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ "መሐረነ" በሚለው የዶ/ር ወዳጄነህ ስም መጠራታቸው ሁሉ ፍቺውን ግለሰቡ እንዳካሄዱት ቍልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው::

## V. አንባቢው ያስተውል!

- ከመጋቢ ሙሉጌታ ግዛት ይልቅ ስለ ወይዘሮ አስቴር መንፈሳዊ ሕይወትና ክርስቲያናዊ ኑሮ ምስክርነት መስጠት ያለባቸው ወ/ሮ አስቴር አባል የሆኑባት የዋሽንግተን ዲሲ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የሆኑት አንፍሬ ዓሊጋዝ እንጂ፣ ጄኔቫ የሚኖሩት እንዲሁም ወ/ሮ አስቴርን በጥቂት ደቂቃዎች ብቻ በመንገድ ዳር እንደ ተዋወቋቸው የገለጹት መጋቢ ሙሉጌታ ግዛት አይደሉም:: የቤተ ክርስቲያን አባልና አገልጋይ የሆኑትን ክርስቲያን እኅት፣ "እግዚአብሔር ተናገረኝ" በሚል "ክፉ መንፈስ አለባት"፣ "የተቅበዘበዘች ሕይወት" ወዘተ ማለት ከነውር ባለፈም መልኩ ትልቅ ወንጀል ሊሆን አይችልምን?
- መጋቢ ሙሉጌታ፣ ወይዘሮ አስቴር ክፉ መንፈስ አድሮባታል በሚል ጋብቻውን ተቃውሚያለሁ ማለት ከዚህም ባለፈ መልኩ "ፍቺው የእግዚአብሔር ልዩ አመራር አለበት" ብሎ ማጽደቅ፣ አገለግለዋለሁ የሚሉትን አምላክና የኑሮዬና የአገልግሎቴ አልፋና ዖሜጋ ነው የሚሉትን ወንጌል በአያሌው የማያስነቅፍበት ምክንያቱ ምንድን ነው?

- *መጋቢ ሙሉጌታ ግዛት፣ "እግዚአብሔር ተናገረኝ" በሚል ፍቺው አምላካዊ ሐሳብ አለበት የሚለው ንግግራቸው "መገለጥ" በሚሉት አገልግሎታቸው ላይ ትልቅ ጥርጣሬ የማያሳድርበት ምክንያት ምንድን ነው? ከመገለጦች ሁሉ በላይ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁም መገለጦች ሁሉ የሚመዘኑበት መገለጥ አሁን ዶ/ር ወዳጄነህ ያደረጉትን ፍቺ ትክክል ነው ይላልን? የማይል ከሆነ የመጋቢ ሙሉጌታ ግዛት የፍቺ "መገለጥ" ከአምላክ የተገኘ ነው ብሎ መደምደም ይቻላልን?*
- *አንድ ሰው ድነት ማግኘቱም ሆነ ያለመዳኑ እግዚአብሔር በመገለጥ ለአገልጋዮች ይናገራልን? መጋቢ ሙሉጌታ፣ "ተናገረኝ" የሚሉት ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ መዳናችንን፣ "መንፈሱ ከመንፈሳችን ጋር በመሆን ይመሰክርልናል" ይላል እንጂ፣ ሌላው ሰው ድነት ማግኘቱንም ሆነ ድነት ያለማግኘቱን መንፈስ ቅዱስ በመገለጥ ይናገራል ማለት "መገለጥ" ተብሎ ከሚጠራው አገልግሎት ዳር ድንበር ውጪ ይመስለኛል፡፡*
- *መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሰው ያልዳነች ሚስት ቢኖረው ይፍታት ይላልን (ወ/ሮ አስቴር አልዳኑም እንኳ ብንል ማለቴ ነው)? አንድ ክርስቲያን ከአንዲት የማታምን ሴት ጋር የገብረ ሥጋ ግንኙነት ቢያደርግ ግለሰቡ ከሴትየዋ ጋር አንድ ሥጋ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርምን?*
- *በመናፍስት ዓለም ያለች ሚስት ክርስቲያን ባሏ ጸልዮም ሆነ መክሮ ዘክሮ ጅኒውን ሊያባርርላት ይገባል እንጂ፣ ክቡር ጋብቻውን ሊያፈርሰው ያስፈልጋል? ሕገ መንግሥትም ሆነ ሕገ አምላክ፣ አንዲት ሴት መናፍስት አለባት ወይም በመናፍስት አሠራር ሥር ነች በሚል ክቡር ጋብቻ መፍረሱን ይደግፋሉን (ወ/ሮ አስቴር ክፉ መንፈስ አለባቸው ቢባል እንኳ ማለቴ ነው)?*
- *ከእኛ ጋር ያለው አምላክ ለመናፍስት አሠራርም ሆነ ለልብ ለውጥ ዐይነተኛ መድኀኒት አለው ብለን እየሰበክን፣ (ያውም ለአንድ መጋቢ ይህ ዐይነቱ ስብከት እንጀራው ሆኖ ሳለ)፣ መጋቢ ሙሉጌታ ይህ ዐይነቱ ችግር ያለባት ሴት የጋብቻ አጋሯ ይፍታት በለው በመየናቸው አግባብነት አለውን?*
- *ዶክተር ወዳጄነህ "ከአፍሪካ መናፍስት" ጋር እንደሚታገሉ ገልጸውልን ሳለ (በመልከዐ ምድር የተገደቡ መናፍስት መኖራቸውን እንኳ በትክክል አላውቅም ነበር)፣ የአንዲት ግለሰብ ያውም የቃል ኪዳን ባለቤታቸውን ክፉ መናፍስት ማባረር አቅቷቸው (ወ/ሮ አስቴር ክፉ መንፈስ አለባቸው ቢባል እንኳ ማለቴ ነው) እርሳቸው ራሳቸው በረው በመሄድ ትዳር ማፍረሳቸው እንዴት፣ "የዚህችን ምድር ማኅተም" ለመፍታት ብቃት አለኝ እንዲሉ ያደርጋቸዋል? የወይዘሮ አስቴርን ማኅተም መፍታት ያቃተው ሰው እንዴት የዚህችን ምድር ማኅተም እንደምፈታ እግዚአብሔር ተናግሮኛል ማለት ይችላል (ወ/ሮ አስቴር በማኅተም የተመሰለ ችግር አለባቸው ብንል እንኳ ማለቴ ነው)?*
- *ባሎች ሚስቶቻቸው በመናፍስት አሠራር ሥር ቢወድቁ ባሎች ሊፈቷቸው ይገባልን?*
- *ሚስት ዓለማዊ እንኳ ብትሆን ክርስቲያን ባሏ ፈቷት እንዲሄድ ቃለ እግዚአብሔር ያስተምራልን?*
- *የእግዚአብሔር ሕዝብም ሆነ ወ/ሮ አስቴር ለዶ/ር ወዳጄነህ ይቅርታ ማድረግ እንደሚገባቸው አምናለሁ፡፡ የዶ/ር ወዳጄነህ ስሕተት ከይቅርታ በላይ ነው የሚል አንዳችም እምነት የለኝም፡፡ ነገር ግን ይህ እውን ሊሆን የሚችለው ዶ/ር ወዳጄነህ አካሄዳቸው ስሕተት እንደ ነበር በውል ተረድረው ይቅርታ ሲጠይቁ እንጂ፣ "በንግግር ጥበብና በሳይኮሎጂ ኀጢአቴን መሰወር እችላለሁ" በሚለው አካሄድ አይደለም፡፡ እርቀ ሰላም እውነትን ማዕከል ያደረገና እውነት*

*የምትጠይቀውን ዋጋ የሚከፍል እንጂ፣ እውነትን አንጻራዊ ምልከታ በማድረግ እውነትን የሚደመስስ ጉዳይ አይደለም፤ ሊሆንም አይገባውም።*

- *ዶክተር ወዳጄነህን እንደ መንፈሳዊ ጀግና ባደረግናቸው መጠን በእኩይ አካሄዳቸው እንዲገፉ ብቻ ሳይሆን፣ ምናልባም ነገ "ካሳዬ ነሽ" የሏትን የዛሬዋን ሚስት፣ በተመደሳሳይ ምክንያት በመፍታት፣ "እግዚአብሔር ተናግሮኝ ነው ፍቺውን የፈጸምሁት" የማይሉበት ምክንያት ምንድን ነው? ፍቺ በአምላክ ዘንድ ጸያፍ ነው የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ገልብጠን ካነበብነው፣ ነገ ፍቺ ውጉዝ ወእኩይ ተግባር ነው ለማለት ምን መሠረት እናገኛለን? እኚህን ግለሰብ ትክክል ናቸው ባልን መጠን፣ ፍቺን እጠላለሁ ያለውን አምላክና የማይገረሠሠውን ቃሉን እያናናቅን እንደ ሆነ ልብ ልንለው ይገባል።*
- *ዶ/ር ወዳጄነህ ይህ ዐይነቱ ሕይወትና ይህን መሰሉ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እያላቸው በየአብያተ ክርስቲያናቱ መድረክ እንዲሰብኩ መጋበዛቸው ትክክል ነውን? እኚህ ግለሰብ በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ ተሰሚነት እንዲያገኙና በርካታ ወጣቶችን በእርሳቸው ጐራ ሥር እንዲያስከትሉ ዕድል የሰጧቸው አብያተ ክርስቲያናት፣ በድርጊታቸው ንስሓ መግባትና በይፋ ይቅርታ መጠየቅ የማይገባቸው ምክንያት ምንድን ነው?*
- *በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ታዋቂ አገልጋዮች ፍቺ እየፈጸሙ ዳግም ጋብቻ በማካሄድ ላይ መሆናቸው በየመጽሔቱ የምናነበው ጉዳይ ሆኖአል፤ ይህ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያናትም ሆኑ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት፣ ጥርስ የሌላቸው አንበሶች እንደ ሆኑ የሚቀጥሉት እስከ መቼ ይሆን? ቅዱሳት መጻሕፍት ተግሣጸ ቤተ ክርስቲያንን በግልጽ እያስተማረ ቤተ ክርስቲያናትም ይህን እውነት እንደሚቀበሉ በአንቀጸ ሃይማኖታቸው ውስጥ እያወጁ ዐዋጁን ተግባራዊ የማያደርጉት እስከ መቼ ነው?*

## ማጠቃለያ

*ብዙ አንባብያን የምታስታውሱት በዚሁ በመዲናችን የተከሠተ አንድ ታሪክ አለ። ቤተ ክርስቲያኒቱ ከየአብያተ ክርስቲያናቱ በተሰባሰቡና በመጋቢው የማስተማር ችሎታ በተማረኩ ወጣቶች የተቈረቈረች ቤተ ክርስቲያን ናት። ብዙዎች፣ "ቤተ ክርስቲያኒቱ የተፈታች፤ ትውልድን ለመቤዠት እግዚአብሔር ያስነሣት ቤተ ክርስቲያን" እንደ ሆነች ይመሰክሩላት እንደ ነበር ትዝ ይለኛል። የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ለወጣቱ ጆሮ የሚጣፍጥ ነገር ግን ለቃለ እግዚአብሔር ፈጹም ባዕድ የሆነ ትምህርት የንግግር ችሎታውን ተገን በማድረግ ያስተምር ነበር።*

*ታዲያ ይህ መጋቢ ይህ ዐይነቱን እንግዳ ትምህርት በሚያስተምርበት ጊዜ ሁሉ፣ "የአዲስ ኪዳን ሐዋርያትም ሆኑ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ይህ እውነት አልበራላቸውም" ማለትን እንደ ፈሊጥ ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ቀኖና ይጠቀምበት ነበር። አንድ ቀን መጋቢው፣ "የአገልግሎት በር ተከፍቶለት" ወደ አውሮፓ ይጓዛል። ከተወሰኑ ወራቶች በኋላ፣ "የሐዋርያዊ ጉዞውን" አጠናቆ ወደ ሸገር ሲመለስ፣ በመጋቢነት ያገለግላቸው የነበሩት ወጣቶች፣ ቤት በመከራየት ጥንድ ጥንድ ሆነው አብረው መኖር ጀምረዋል። መጋቢው ይህ ሁኔታ ስላልተዋጠለት፣ "ተቃራኒ ጾታ ጥንድ ጥንድ ሆኖ አብሮ መኖር ቅድመ ጋብቻ ወሲብ ስለሚሆን ዝሙት ነው" ሲል ድርጊታቸውን ይኰንናል። ወጣቶቹም በአንድ ድምፅ፣ "ይህ እውነት ለአንተ አልበራልህም" ሲሉ አጸፋዊ ምላሽ ይሰጡታል።*

ዛሬ በሰላሙ ጊዜ ይበጀኛል በሚል፣ በብልጣብልጥነት ያፈረስነው ሕገ እግዚአብሔር፣ ነገ በአጣብቂኝ ወቅት እንጠቀምብህ ቢሉት ፈርሶአልና አያገለግልም፡፡ ቃለ እግዚአብሔርን በምናፈርስበት ጊዜ ሁሉ ደግሞ፣ ሕገ መለኮትን ማፍረሳችን ብቻ ሳይሆን፣ ከዚህ ሕይወት ከሚቀዳበት ሕግ ራሳችንን ማግለላችንና ተቃራኒ የሆነውን የጨለማውን አሠራር በሕይወታችን ውስጥ እያስተናገድን መሆናችንን መዘንጋት የለብንም፡፡ ዛሬ "የተማሩ የተመራመሩ" ሰዎች ስለሆኑ ብቻ፣ "የእግዚአብሔር ልዩ ዐላማ አለባቸው" እያለን እኩይ ድርጊታቸውን የማንኰንን እንዲያውም የምንደግፍ ከሆነ፣ ነገ እኩይ ምግባርን ለመኰነንም ሆነ ሠናይ ምግባርን ለመሸለም አንዳችም መሠረት እንደማይኖረን ልናውቀው ይገባናል፡፡

በርግጥ ዶ/ር ወዳጄነህ ትዳራቸውን እንዲያፈርሱ ያደረጋቸው እስካሁን ያየናቸው ምክንያቶች ከሆኑ፣ "በዚህች ምድር ላይ የታረዱት" እርሳቸው ሳይሆኑ ወ/ሮ አስቴር ናቸው፡፡ ዶ/ሩ ዐረዱ እንጂ አልታረዱም ያውም ዕርዱን ያካሄዱት እርሳቸው ራሳቸው፣ "ጌሜም የእግዚአብሔር መድረክ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ" ባሉት ክርስቲያናዊ መጽሔት እንዲሁም የእውነት ዐምድ በሆነችው በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው፡፡

“በእኔ ላይ የደረሰው ግፍ በማንም ሴት ላይ እንዲደርስ አልፈልግም” የሚለው የወ/ሮ አስቴር ንግግር፣ ብዙዎቻችን የምንጋራው ጕዳይ ይመስለኛል፡፡ ይህ ዐይነቱ ግፍ በሴት እኅቶቻችን ላይ እንዲደርስ መፈለግ ብቻ ሳይሆን መፍቀድ የለብንም፡፡ በተለይ የእውነት ዐምድ የሆነችው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ይህን እኩይ ድርጊት በአንድ ድምፅ መኰነን ይጠበቅባታል፡፡ “እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው” (ማቴዎስ 19÷6፤ ማርቆስ 10÷9)፡፡ ውድ እኅታችን ወ/ሮ አስቴር በደረሰብዎ ግፍ ብዙዎቻችን እጅግ፣ እጅግ፣ እጅግ አዝነናል፡፡ የምድር ሁሉ ፈራጅ እግዚአብሔር ሐዘኖትን እንዲያስረሳዎ ምኞቴና ጸሎቴ ነው፡፡ ጌታ በነገር ሁሉ ይባርክዎ፡፡

## ማሳሰቢያ

ይህ ጽሑፍ በዚህ መልኩ ለንባብ ከመቅረቡ በፊት፣ የጽሑፉ አዘጋጅ ጽሑፉን ዶ/ር ወዳጄነህ አንብበው አስተያየት እንዲሰጡበት ተደጋጋሚ ጥረት አድርጓል፡፡ ይህን አካሄድ መከተል የተፈለገበት ምክንያት ሚዛናዊ የሆነን ነገር በአንባቢው ጆሮ ለማድረስ ነው፡፡ ዶ/ር ወዳጄነህ ጽሑፉ ከተላከላቸው ጽሑፉን አንብበው አስተያየት ለመስጠትም ሆነ ለመወየየት ሙሉ ፈቃደኛ እንደ ሆኑ የገለጹ ቢሆንም፣ ጽሑፉ ከተላከላቸው በኋላ ግን፣ በጽሑፉ ላይ አሉ የሚሏቸውን ስሕተቶች አንድ በአንድ እየነቀሱ በማውጣት ውይይት ፈቃደኛ ያለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ አላስፈላጊ የሆኑ ትርፍ ንግግሮችን ተናግረዋል፡፡ ዶ/ር ወዳጄነህ ከጸሓፊው ጋር ያደረጉት ውይይት በተንቀሳቃሽ ስልክ ተቀርጾአል፡፡